# የመሬት ጉዳይ በኢትዮጵያ

አስራት አብርሃም

እነሆ በኢትዮጵያ ምድር "የመሬት ላራሹን" መፈክር በኢትዮጵያ ተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘመሩበት ወቅት ግማሽ ክፍለ ዘመን ሊሞላው የቀረው ጥቂት ዓመታት ቢሆንም አሁንም ድረስ የመሬት ጥያቄ በኢትዮጵያ ምላሽ ያገኘ ጉዳይ አይደለም፡፡

ሶስተኛው የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት እየተባለ የሚጠራውና የኢህአዴግ መራሹ መንግስት ርዕዮተ ዓለም እንዲያንፀባርቅ ሆኖ የረቀቀው "የኢትዮጵያ ፌዴራለዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት" አንቀፅ 40 ተራ ቁጥር 3 ስለመሬት ባለቤትነት ያሰፈረውን ስንመለከት፣
**"የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፥ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡"**
የሚል እናገኛለን።

ሕገ መንግስቱ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ "የመንግስት፥ የብሄሮች፥ የብሄረሰቦችና የህዝቦች የጋራ ንብረት ነው" ቢልም ከአባባሉ ጀምሮ እስከ በተግባር እየሆነ ያለው ነገር በጣም ብዙ የሆኑ እርስ በእርስ የሚጣረሱ እውነታዎች ያሉበት ነው፡፡
በዚህ አባባል መሰረት መንግስት ራሱን ችሎ የመሬት ባለቤትነት ድርሻ የሚኖረው እንዴት ነው የሚል ጥያቄን የሚያስነሳ ነው፡፡ ምን ያህሉን ድርሻስ ነው የሚኖረው በግልፅ የተቀበጠ ነገር የለም!

ብሄሮች፥ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የሚሉት አባባሎች ፕሮፌሰር መስፍን እንደሚሉት ንምን ትርጉም የሌላቸው አንድም ሶስተም የሆኑ እሳቤዎች ናቸው ወይስ ምን ያህል ግልፅና የማያሻሙ ልዩነት አላቸው፡፡ የትኞቹ ናቸው ብሄሮች የትኞቹ ናቸውስ ብሄረሰቦች የትኛቹስ ናቸው ህዝቦች የሚባሉት በተለይ ለኢህአዴግ ርዕዮተ ዓለም የሄድን እንደሆነ ህዝቡ በብሄረሰብ ምልከታ አንፃር ነው ተከፋፍሎ የተመደበው፡፡ ከዚያ ውጭ የሆነ ኢትዮጵያዊ እንደሌለ በቀላሉ ቀበሌ ሄደህ መታወቂያ ስታወጣ ብሄር የሚለውን ከፍት ቦታ የግድ መሙላት እንዳለብህ ሲገርህ ነው የበለጠ ግልፅ የሚሆነው፡፡ እናም ህገ መንግስቱ "ብሄር" ብሎ "ብሄረሰብ" ካለ ኋላ "ህዝቦች" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ ቅልቅል ለሆኑ ኢትዮጵያውያን እውቅና ስለማይሰጥ ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ "ህዝቦች" በሚል ስም የመሬት ባለቤትነት መብት የሰጣቸው እነማን ናቸው የሚል ጥያቄም ጭምር ነው የሚያስነሳው፡፡

የሆነ ሆኖ ሕገ መንግስቱ የሚለውን እንዳለ እንቀበለውና በዚህ ህገ መንግስት መሰረት አንድ ኢትዮጵያዊ የመሬት ባለቤት መሆን እንደሚገባው የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአንዱ ወይም በሌላው ብሄር ወይም ብሄረሰብ ወይም ህዝቦች ውስጥ ሊታቀፍ ስለሚችል እና መሬት ደግሞ የብሄሮች፥ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ስለሆነ የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል

ማለት ነው፡፡ በዚህ ስሌት ከሆነ በገጠር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ የእርሻ መሬት በከተማ የሚኖው ደግሞ የመኖሪያ ቤቱን የሚሰራበት መሬት የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት አለው ማለትይሆናል፡፡

አሁን ደግሞ በተግባር እየሆነ ያለው ነገር እንመልከት ለምሳሌ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የመሬት ድልድል የተደረገው በ1979 ዓ/ም ነው አከባቢ ይመስለኛል፡፡ የዛን ጊዜ ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የነበረው ዜጋ መሬት አልተሰጠውም ነበር፡፡ ያዜጋ ዛሬ ዓርባ ዓመት ቢሞላውም ትዳር መስርቶ ቤተሰብ ቢያፈራም አሁንም ድረስ የቤተሰቡ ጥገኛ ነው፡፡ በአጭሩ ከዓርባ ዓመት በታች ያለው ሁሉ መሬት የለውም ወይም በቤተሰቦቹ ላይ ጥገኛ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ በፐርሰንት ሲሰላ የህዝቡን 60% ያህል ነው፡፡ ወደ ከተማ የመጣን እንደሆነ ደግሞ መሬት በሊዝ ወይ ለፖለቲካውና ለስርዓቱ ባለው ቅርበትና ርቀት የሚወሰን ነው፡፡

በተግብር ሲታይም መሬት የስርዓቱ ካድሬዎችና የመንግስት ባለስልጣናት ነው የሆነው፡፡ መሬት በሊዝ እና በሌሎች ልዩ ልዩ መንገዶች ይቸበቸባል፡፡ በህግ መንግስቱ መሬት እንደማይሸጥና እንደማይለወጥ ቢደነገግም ስርዓቱ አንዴ በሊዝ ሌላ ጊዜ በሌላ ምክንያት መሬት ለፈለገው ወገን ሲያድል ነው የሚታየው፡፡ እንደአንዳንድ ሰዎች እምነት ከሆነ መሬት ለመቶ ዓመታት ያህል በሊዝ መስጠት ከመሸጥ የማይተናነስ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ገበሬ ያለውን እዚህ ላይ ብጠቅሰው በጣም ደስ ይለኛል፡፡ “እኔ አንዲት ላም አለኝ ልብል በሊዝ ለአምሳ ዓመታት ባከራያት፤ ከአምሳ ዓመት ኋላ ወይ አጥንቷን ወይ ቆዳዋን ብቻ ነው የማገኘው” በማለት የስርዓቱ የሊዝ ፖሊሲ ምን ያህል የተሳሳተ እና ጎጂ መሆኑን አስቀምጧል፡፡

ከሁሉም የሚገርመው ነገር ደግሞ በወለጋ በጋንቤላ በቤንሻንጉልና በሌሎች የአገራችን አከባቢዎች ያሉት በጣም ለም የሆኑ መሬቶች ለአንድ ካሬ ሜትር ስኴር ከአምስት ደላር በታች ለዓመት የሚከራይ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ የሚገኘው ገቢ ደግሞ ጊዜያዊ የውጭ ምንዛሬ ማስገኛ ሆኖ ያገለግል እንደሆነ እንጂ ለህዝቡና ለአገሪቷን የሚያስገኘው የረባ ጥቅም እንደሌለው ግልፅ ነው፡፡ በዚህ ላይ ከመሬቱ የሚገኝ ምርት ሁሉ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የማይውልና በቀጥታ ወደ ውጭ ተጭኖ የሚሄድ ነው፡፡ በረሀብና ቸነፈር ለሚሰቃየው የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚሁ መና የሚቋደስበት ዕድል አይኖርም ማለት ነው፡፡

ሌላው በጣም አከራካሪው ጉዳይ የከተማ መሬት ነው፡፡ ይህም ብር ለሚያሳይ ሁሉ በፈለገው ቦታ በዚያ የሚኖሩትም ዜጎች ጭምር በማንሳት ይሰጠዋል፡፡ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ከተማ ያለው መሬት በዚሁ መልክ እየተበቸበ ነው ያለው፡፡ በሊዝ ሊገዛ ለፈቀደ ሁሉ ፈረንጅ ይሁን ሀበሻ በፈለገው ቦታ በዚያ መሬት ላይ የሚኖሩትን ህዝቦች ሁኔታና ዕድል ከግምት ውሰጥ ሳይገባ ነው መሬቱን የሊዝ ሽያጭ የሚካሄደው፡፡ አንድ አባት ስርዓቱን በመሬትና በአገር ሉኣላዊነት ላይ ያለውን አቋምና አመለካከት ሲተቹ፤ “ስርዓቱ ልክ የባርሌዲ ዓይነት ነው፡፡ ምንና ለማን መስጠት

**እንዳለበትና እንደሌለበት እንኳ ለይቶ የሚያውቅ አይመስልም፡፡  ብር ይዞ ለመጣ ሁሉ አንስቶ መስጠት ብቻ ነው የሚያውቀው”** በማለት ነው ሀሳባቸውን በአጭሩ የሚያስቀምጡት፡፡  ይህ በራሱ መንግስት በመሬት ላይ ያለው አሰራር በመርህና በሞራል ላይ ተመስርቶ እንደማይጓዝ የሚያመለክት ነው፡፡

በተለይ አሁን በከተሞችና በከቶሞቹ አዋሳኝ በሆኑ አከባቢዎች ያለው የመሬት ቅርምት ጉዳይ መቼውም ታይቶ የማይታወቅ ነው፡፡ በእነዚህ አከባቢዎች ያሉት የመንግስት አስተዳደሪዎች መሬቱ ሲሸጥና ሲለወጥ፥ ቤቶች ሲሰሩበት፥ ወደ ከተማነትና ሰፋፊ መንደሮች አስኪቀረዩ ቁጭ ብለው ለዓመታት ሲመለከቱ ይቆዩና ድንገት በሆነ ጊዜ ተነስተው “ህገ ወጥ መንደሮች ናቸው” በማለት በዶዘር ወደ ማፍረሱ ይገባሉ፡፡

አሁን በመቀሌ ከተማና አከባቢዋ እየሆነ ያለው ይሄ ነው፡፡ በእዚች ከተማ ላይ እየተፈፀመ ያለው ነገር በጥልቀት የተመለከትነው እንደሆነ ለየት ያለ ገፅታ ያለው ይመስላል፡፡ በእርግጥም ይህ ችግር በሌሎች ከተሞች ከዚህም እጅግ የባሰ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ እኔ በቅርበት የታዘብኩትን ላስቀምጥ፤

1. በከተማው ዙሪያ ካሉት ነባር ይዞታዎች ሰዉ መሬት ሲገዛ፥ ሽያጭና ገዝ ውሉን የሚያፈፅሙት በየአከባቢው ያሉት ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ያው የመንግስት ታችኛው መዋቅር አካል ናቸው፡፡ ስለዚህ መንግስት በጉዳዩ ላይ እጁ እንደነበረበት የሚያመለክት ነው፡፡

2. እነዚህ ቤታቸው እንዲፈርስ የተወሰነባቸው በብዚ ሺህ የሚቆጠሩ ኗሪዎች ቤቶቹን ለመስራት በአሁን ባለው የኑሮና የህንፃ መሳሪያዎች ውድነት ምን ያህል ጥሪት እንዳፈሰሱበት ለመገመት የሚከብድ አይደለም፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን አንድ አባት ልጥቀስ እኚህ አባት አስር አለቃ ስንታዮህ ሀብቲይመር ይባላሉ፡፡ ዕድሜያቸው ሙሉ ወታደርና ፖሊስ በመሆን ለዚች አገር ሲያገለግሉ ኖረው፤ በጡረታ ከተገለሉ ኋላ ሎተሪ በማዞርና ሌሎች የጉልበት ስራዎች እየሰሩ ነው የሚተዳደሩት፡፡ በዚህ መንገድ አጠራቅመው የሰሩት ቤት አሁን እንዲፈርሱ ከተወሰነባቸው ቤቶች አንዱ ሆኗል፡፡ ቤቱ እየተባለ እንዳለው የሚፈርስ ከሆነ የእኚህ አባት ቤተሰብ የትነው የሚገባው! ጎደና  ተዳዳሪ ሊሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ መንግስት ለእንዲህ ላሉ ዜጎች ችግር የሚሆን መፍትሄ አለው?!

3. ሌላው የህንፃ መሳሪያዎች ጉዳይ ነው፡፡ በመቀሌ ውስጥ ስሚንቶ ከመሰቦ ፋብሪካ የሚወጣው በ170 ብር ነው፡፡ ጉና የተባለ ድርጅት ተቀብሎ በገዠው ፓርቲ ርዕዮተ ዓለም ቅኝት ለተቋቋሙት ጥቃቅንና አነስተኛ የስሚንቶ ቸርቻሪዎች ያከፋልላቸዋል፡፡ ከዚያ እነሱ ደግሞ ለነጋዴዎች ያከፋፍሉታል፡፡ ነጋዴች በተራቸው ለህዝቡ ይቸረችራሉ፡፡ ከፋብሪካው ወጥቶ ወደ ተራው ህዝብ እስኪደርስ መጨረሻ ላይ ዋጋ ወደ 470  ይደርሳል፡፡ ከ170-470 ብር ጭማሪ የሚያሰየው ስሚንቶው

ከፋብሪካው መጋዘን ሳንይቀሳቀስ በኩፐን ግገር ብቻ ነው እየተቀባበሉ የሚያተርፉበት፡፡ ይህን ጉዳይ አንስተው አቶ ስዬ ባለፈው በመቀሌው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ሲናገሩ “በራሳችን አፈር፥ በራሳችን ከተማ እየተመረተ እንዴት እዚህ በዚሁ ይህን ያህል ውድ ሆኖ ይሸጣል” ነበር ያሉት፡፡ እነዚህ አሁን እንዲፈርሱ የተወሰበቻቸው ቤቶች ደግሞ ስሚንቶ በዚሁ መልኩ በሚቀርብ ውድ የሆነ ሁኔታ ነው ገዝተው የሰሩት የድሆችና የምንዱባን ቤቶች ናቸው፡፡

4. የክልሉ ባለስልጣናት ቡቡ በሚባል የከተማው እስትራተጂካዊ ቦታ ያውም ለከተማው ውበትና አየር ፀባይ ጥበቃ ተብሎ በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት ለደን ልማት በተተወ መሬት ላይ ከተወሰኑ ነጋዴዎች ጋር ተሳጥረው አምስት መቶ ካሬ እያንዳንዳቸው ከአሁን በፊት በመውሰዳቸው ምክንያት ይህ ጉዳይ በግምገማ ታይቶ ስህተት መሆኑን ታምኖበት እንዲቆም ከተወሰነ ኋላም ቤቶቹ በአውሮፓ እስታይል መሰራታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ይህን የታዘበው የከተማው ህዝብ ደግሞ “የሙስና ሰፈር” በማለት አከባቢው ሰይሞታል፡፡ እንግዲህ ማስተር ፕላር ሳይቀር ለደን በከለለው መሬት ላይ ለራሳቸው ሕገ ወጥ ቤት እየሰሩ ድሃው ህዝብ ለዘመናት አጠራቅሞ የሰራውን ቤት እንዲፈርስ ሲወስኑ በዚህ አገር ያለው ሕግ ለባለስልጣናትና ለተራው ዜጋ እኩል የሚሰራ እንዳልሆነ የሚያመላክት ከሆኑም በላይ የሚገርምና የሚደንቅ ነው ነገር ነው የሚሆነው፡፡

ይህ ዓይነቱ ብልሹ አሰራር የፈጠረው ብሶት ነው እንግዲህ ትናንት ሚያዚያ 12/2003 ዓ/ም በመቀሌ ከተማ “ማይ አንበሳ” እና “ገፊሕ ገረብ” ከሚባሉ አካቢዎች የተነሱ ሰላማዊ ሰልፈኞች በአከባቢያቸው ለሚገኘው የቀበሌ አስተዳደር ቢያለከቱም ተገቢ የሆነ መልስ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ወደ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት በማምራት ላይ ሳሉ መንገድ ላይ በፌደራል ፖሊስ ተከበው እንዲቆሙ ከተደረገ ኋላ “**እያደረጋቸሁት ያለፍ ሰልፍ ሕገ ወጥ ነው፡፡ ወደ መሀል ከተማ እንገባለን፥ ሰልፉንም እንቀጥላለን ካላችሁ ግን አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን**” በማለት ሰልፈኞቹን ለማስፈራራት ከጣሩ ኋላ ህዝቡ ባለበት ለመቆም ተገዷል፡፡ ከዚያ ኋላ የሚመለከታቸው ባለስልጠናት መጥተው በጉዳዩ ላይ ከህዝቡ ጋር ለመወያየት እንደሚፈልጉ ገልፀው ቀን ተቆርጦለት ሰልፎኞቹም በዚህ ዙሪያ ያለውን ጉዳይ የሚከታተሉላቸው ተወካዮች እዚያው እንዲወክሉ ተደርጎ ህዝቡ ለጊዜው ወደ የቤቱ እንዲሄድና ሰልፉን እንዲበተን ተገርጓል፡፡

ሰልፉን ሲከታተል የነበረው የጥሕሎ መፅሔት ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ ሲቀርፅበት የነበረውን ካሜራና ሞባይል ስልኩን ቀምተው ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዱትና ያን ዕለት ማታም ከነካሜራው እንደተለቀቀ በፌስ ቡክ ባሰራጩው ፅሁፍ ላይ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ሃለቃ ትርፊ ሀዱሽ የተባሉ የዓረና አባል ሰልፉን በቪድዮ እያስቀረፁ ሳለ ተይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከተወሰዱ ኋላ የቀረፁትን ፊልም ሁሉ ተቀምተው በ2000 ብር ዋስ ማታውኑ ተለቀዋል፡፡ ሁለት መቀሌ የሚገኘው የፎቶ ድሬ ካሜራማኖችም እንደዚሁ ሲቀርፁ ተይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከተወሰዱ በኋላ የቀረፁትን ፊልም ተቀምተው ስማቸውንና አድራሻቸውን እንዲመዘገብ ተደርጎ በተመሳሳይ ሰዓት ከአለቃ ትርፊ ሀዱሽ ጋር ተፈተዋል፡፡

ይህ የመቀሌው የሰላማዊ ሰልፍ ሙከራ በቀጥተኛ ትርጉሙ ካየነው ፖለቲካዊ ይዘትና ግብ ላይኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን በመቀሌ ከተማ እንዲህ ዓይነቱን ሰልፍ ሲሞከር ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ አርአያነቱ የጎላ ነው የሚሆነው፡፡ ህዝብ ሲበደልና ፍትሕ ሲያጣ እስከምን ድረስ ሊሄድ እንደሚችል አቅጣጫ የሚጠቁምና ለስርዓቱም ግልፅ የሆነ መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው፡፡

በሰሜን አፍሪካ ህዝባዊ ማዕበል እንዲጀመር ምክንያት የሆነው አጋጣሚ ሁላችንም የምናውቀው ነው፡ ፡ የአንድ ተራ አትክልት አዟሪ ድንገተኛ መስዋዕትነት የፈጠረው ነው፡፡ ያን ጊዜ መህመድ ቦአዚ ራሱን በጋዝ ራሱን ሊያቃጠል ሲወስን የስርዓት ለውጥ አመጣለሁ ብሎ አልነበረም፡፡ የእርሱን መስዋዕትነት ያንገበገባቸውና ስርዓቱን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ብርታት የሰጣቸው ቱኒዚያዊያን ናቸው የተቃውሞውን ግብ የስርዓት ለውጥ እስከማጣት ድረስ እንዲሄድ የገፉበትና በመጨረሻም ተሳክቶላቸው ቢን ዓሊን ከነቤተሰቡ እና ከነስርዓቱ ለዘላለሙ ለመሸኘት ያቻሉት፡፡ ይህን ክስተት በአንክሮና በቅርብ ሆኖ ሲከታተል የነበረው ግብፅ ህዝብም በተራው የራሱን አምባገነናዊ ስርዓት ለማስወገድ በቱኒዚያውያኑ መንገድ ለመጓዝ ወስኖ ጊዜም ሳያባክን በአንድነት ሆኖ ወደ ታህሪር አደባባይ ተመዋል፡፡ ስርዓቱ እጁ እስኪሰጥ ደረስም እዚያው ከትሞ ትግሉን መርተዋል! አስተባብረዋል! እነሆም ግብፅ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለሳላሳ ሁለት ዓመታት ተደላድሎ ሲገዛት የነበረው የሁስኒ ሚባረክ ቤተሰባዊ አገዛዝ ነፃ ወጣች፡፡ ድሮ እንኳ ሕገ መንግስታዊ መሻሻያ ላይ ሪፈረንደም በማካሄድ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሽግግር በድል እየተጓዙ ነው ያሉት፡፡ እውነትም ግብፆች ታላቅ ህዝቦች ለመሆናቸው ዳግም አስመሰከሩ፡፡ በተገኘው ድል ሳይዘናጉ አብዮቱን እንዳይቀለበስ ሌት ተቀን እየጠበቁት ነው፡፡ በአዲሱ ጊዚያዊ ባለአዳራ ወታደራዊ መንግስት የተዛነፈ ነገር ያለ መስሎ ሲታያቸው ወዲያው ወደ ታህሪር አደባባይ ወጥተው ድምፃቸውን ያሰማሉ!

እነሆ በዚህ ዘመንም ተአምር ሆነ! መሀመድ ቦአዚ ዓለምን ወደ አንድ የተሻለ ምዕራፍ የሚያሸጋግር የለውጥ መልዕክተኛ ሆኖ መጣ፡፡ የመሀመድ ቦአዚ ተፅዕኖ ከአሁን በፊት ከነበሩት ታላላቅ ሰዎች ሁሉ የተለየ ሆኖ ቃላዊ ተስፋና ፕሮፓጋንዳ መንዛት ሳይጠበቅበት፥ ክላሽንኮብ አንግቦ ጋራና ሸንተረር መውጣት ግድ ሳይለው፥ በአቋራጭ ራሱን በእሳት በማንደድ ብቻ ብርታትንና ነፃነትን ለተጨቆኑ ህዝቦች ሁሉ አምጥተዋል፡፡

ድል ለቦአዚ አብዮት! ሽንፈት ለአምባገነኖች ይሁን!